# አነሁላይዋ “አንቀፅ ሰላሣ-ዘጠኝ”!

*የግል አስተያየት፦ በአያል ሰው ደሴ*

“5 ኛው ዓለም-አቀፍ የፌዴራሊዝም ጉባዔ” በሚል ርዕስ አስገራሚና አሣሣች የኢሕአዴግ ድግስ በአገራችን ዋና ከተማ በአዲስ-አበባ በቅርቡ ተከናውኗል፡፡ ይኸ ትዕይንት በአጭሩ እንደ-ማንኛውም የአገዛዙ ይፋዊ እርምጃዎች ሁሉ የገዥዎቹን የውዥንብር የፖለቲካ ፍልሥፍናና ቋንቋ/ብሔረሰብ/ጎሣን መሠረት ስላደረገው ክልላዊ የመንግሥት አወቃቀር “እንከን-የለሽነት”፣ “ትክክለኛነት” እና “ጠቀሜታ” እራሣቸውን አሳምነው በሌሎቻችን (ሕዝቡ) ላይ ያለውን አስተጋቦ ለማስረገጥ፣ ቀጣይ አፍራሽ እቅዶቻቸውን ለማደላደልና ለለውጥ ፈላጊው ወገን ተጨማሪ መራኮቻ የቤት ሥራ ለመስጠት ታስቦበት የተደረገ አደንቋሪና አደናጋሪ ክንዋኔ ነው፡፡

መቸም ስለ ፌዴራላዊ ሥርዓት ምንነትም ሆነ ያም ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአገራችን ላይ ከጫነው የዞረበትና የተወናገረ የአገዛዝ ሥርዓት ጋር ያለውን ልዩነት በተመለከተ፣ አልፎም ይኸ አሁን ሕዝባችንን ለሰቆቃ የዳረገና እጅጉን ለባሰ ችግር እያመቻቸ ያለ የመንግሥታዊ አወቃቀር ፍልሥፍና ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ጀምሮ እስከ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ድረስ በድርጅት ደረጃ በሠፊውና በዝርዝር የተተቸበት፣ በርካታ ምሑራንም አስተያየቶቻቸውን የሰጡበት ስለሆነ እዚኸ ላይ ልዘረዝር አልሞክርም፡፡ የሆነ ሆኖ በአገራችን ሁሉም አትራፊና ተጠቃሚ ለሚሆንበት፣ ፍትኅን፣ እኩልነትንና አንድነትን ሊያረጋግጥ ለሚችል ሕዝባዊ ሥርዓት ለሚደረገው ቀጣይ ትግል እክል ከሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች መኻል አሁን በአገራችን ላይ የተጫነውና እንዲሠራ እየተደረገ ያለው “ሕገ-መንግሥት” መሆኑን ግን ሳላሰምርበት አላልፍም፡፡ ይኸ የአገሪቱ ልዕለ-ሕግ እንዲሆን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫነ ሰነድ የሕወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጧል፡፡ የፖለቲካውን ሂደት በቅጡ የተረዱና ጉዳዮችን በብስለትና በሰከነ-መንፈስ የሚያዩ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖች ይኸን “ሕገ-መንግሥት” ገና ከረቀቃው ጀምረው ታግለውታል፣ አደገኛነቱንና መዘዙን ሳይታክቱ አመላክተዋል፡፡

በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ አንዳችም ማሻሻያ ያልተደረገበትና እንደማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት በቀላሉ እንዳይሻሻል ተደርጎ ተቆልፎ የተዘጋጀው ይኸ ሰነድ የአገዛዙ ፍልሥፍና ዋነኛ መሠረት ነው፡፡ ስለሆነም ነው የአገዛዙ ቁንጮዎች በዚኸ ሰነድ ላይ የሚደረግን ማንኛውም ትችት በቀላሉ የማያዩትና እያንዳንዱ ነቀፌታ የሚይዙትን እስከሚያጡ የሚያሸብራቸውና አጥብቆ የሚያወራጫቸው፡፡ ይኸ ሰነድ እስካለ ድረስም መንግሥታዊ ሥልጣን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ እጅ፣ ጠቅላይ ሚኒስትርነትም ድንገት “በጎ-ፈቃዳቸው” ካልሆነ በስተቀር በዕድሜ-ይፍታኅ ትሥሥር ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ተቆራኝቶ የሚቀጥለው፤ አገዛዙም አንቀፅ ጠቅሶ እንደ-ፈለገው ዜጎችን ለማሰርም፣ ለመውረስም ማንገላታቱን እንዲቀጥል፣ ገዥዎቹ “አስፈላጊ” ሆኖ ያገኙትን ማናቸውንም፤ ለምሣሌ መሬት የመሸጥን፣ ድንበር ቆርሶ ለባዕዳን የመስጠን፣ የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል ለውጭ ጥቅም “የማከራየትን“፣ ወዘተ የመሣሰሉ ከባድ ከባድ ጉዳዮች ሣይቀሩ ሕዝብ ሳይመክር ይሁንታውንም ሣይሰጥ እንዳሻቸው ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ ስለሆነም ነው ትግላችን ትርጉም እንዲኖረውና ለውጡም መሠረታዊ እንዲሆን ከተፈለገ ይኸን “ሕገ-መንግሥት” የተባለውን የአገዛዙ መዘዘኛ መሠረት ጠንቅቆ ማወቅና በአንድ የጠራ ልቦናና ቁርጠኝነት ለማስወገድ ቆርጦ መነሣት የሚያስፈልገው፡፡ አዎን ነገሩ ቀላል አይሆንም፡፡ አሁን በተቃማዊው ጎራ ተሰልፈናል ከሚሉት ውስጥ ምን ያኸሉ 'ችግራቸው ከ“ሕገ-መንግሥቱ” ሣይሆን ከአገዛዙ' እንደሆነ የሚያምኑና አቋማቸውን ግልጥ ያደረጉ እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ ምናልባትም የፖለቲካውን የነገር ብልትና የአገዛዙን መሠረታዊ የፖለቲካ ፍልሥፍና በውል ከተረዱ ጥቂቶች በስተቀር አብዛኞዎቹ በዚኸ የብዥታ ባሕር ውስጥ የሚዋኙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

የአገዛዙ ቁንጮዎች፣ ዋና የፖለቲካ-አቀንቃኞቻቸው (ካድሬዎቻቸው) እና አድር-ባይና ጌታ-አደር ግልብ "ምሁሮች" ሥርዓቱ ይኸን "ሕገ-መንግሥት" ተከትሎ አገሪቱን ቋንቋን/ጎሣን መሠረት ያደረገ መንግሥታዊ አወቃቀር በመከተሉ ምን ያኽል "ብሔሮች፣ ብሔረ-ሰቦችና ሕዝቦች" "መብቶቻቸው እንደተከበሩ"፣ አልፎም የአገሪቱን አንድነት ማቆየት መቻሉን፣ ወዘተ.. በንቀታዊ ድፍረት እጅ-እጅ የሚል አጥወልዋይ ስብከታቸውን ሲያስተጋቡ ኖረዋል፤ አሁንም ከላይ በተጠቀሰው ጉባዔ ላይ ይኸንኑ አደንቋሪ የቅጥፈት ሰበካ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ለፍፈዋል፡፡ ምንም ዓይነት ታሪካዊ ጭብጥነትም ሆነ አንጻችም ተኣማኒነት በሌለው፣ በማንኛውም አገር ታይቶና ተሰምቶ በይታወቅ መንገድ አንድን አገር በትኖ፣ የሕዝብን ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ሥነ-ልቦናዊ የትሥሥር ገመዶች በጣጥሶ፣ ሕዝብ በአንድ አገር ዜግነቱ እንዳያስሣብና በቡድን ታጥሮ እንዲኖር ለማድረግ አንድነቱ እንዲጠፋና ተለያይቶ እንዲያድግ ለማድረግ እየደነደነ የሚሄድ የጎሣ የልዩነት አጥር በመስራትና እየቆየ የሚጎን ፈንጅ በመቅበር ከላይ ተንከራፎ በተቀመጠ ውሽልሽል ጣራ አዋቅረው የአገር አንድነት አስገኝተናል ማለት አንድም የድንቁርና የመጨረሻው ደረጃ ነው አለያም የለየለት ትዕቢት ነው፣ አለፍ ሲልም አገርን ሆን ብሎ ለማፈራረስ የሚደረግ መሰሪ ቅጥረኝነት ከመሆን አያልፍም፡፡ ያም-ሆነ-ይኸ ድርጊቱ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የተፈጸመ ደባ ነው፡፡

ብዙ ወገኖች የዚኸን "ሕገ-መንግሥት" ጎፀዕ የሚያዩት ወይም አደገኛነቱን የሚለኩት ከአንዲት አንቀፅ ከ"አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ" አኳያ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የሆነ-ሆነ የዚኸ ሰነድ አፍራሽነትና አዲስነት የሚጀምረው ግን ገና 'ሀ' ብሎ ሲነሣ ከመግቢያው ነው፡፡ የችግሩ ዋልታ ያለው የአገዛዙን መሠረታዊ ፍልሥፍና ገላጭ ከሆነውና የዜጎችን ሉዓላዊነት ከጣሰው፣ አሣልፎ ከሰጠውና የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ከናደው መንደርደሪያ ላይ ነው፡፡ "አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ" ሆነ ሌሎቹ ሁሉ ከዚኸ መሠረታዊ እምነት የፈለቁና የተመነዘሩ ናቸው፡፡ ይኸ አገዛዙ የሚደነፋበትና አድር-ባዮች ወይም ተላሎች የሚኮፈሱበት "ሕገ-መንግሥት" በማንም እንደ ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪና ልዩ ልዩ ባኅሎችና ሐይማኖቶች ባለቤት ዜጎች ያሉባቸው አገሮች ውስጥ አይገኝም፡፡ የተወሰኑ ምሣሌዎችን እንይ፤

ሀ) ሕንድ፦ እንደ-ኢትዮጵያ በኅብራዊነት የታደለችው ሕንድ ሕገ-መንግሥቷ የሚጀምረው እንደኛዎቹ ግብዞች "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች (We, the Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia " ብሎ ሣይሆን "እኛ የሕንድ ሕዝብ . ( WE, THE PEOPLE OF INDIA,... ) ብሎ ነው፣

ለ) አሜሪካኖች አሥራ-ሦስት እራሣቸውን የቻሉ የእንግሊዝ ቅኝ-ግዛቶችን አንድ ላይ በማምጣት አንዲት አገር ሲመሠርቱ እንኳ ያወጡትና የሚተዳደሩበት ሕገ-መንግሥት የሚጀምረው "እኛ የአሜሪካ ሕዝብ… (We, the people of the United States,...) በሚል ነው፡፡

ሐ) የተወሰነው ያውም አናሣው ወገን (ነጩ) አብዛኛውን (ጥቁሩን) ሕዝብ ሰው የመሆን መብቱን ጭምር በነፈገ ዘግናኝ የአፓርታይድ ዘረኛ ሥርዓት ፍዳውን ያየ ሕዝብ ያለባት፣ በውስጥም በርካታ እምነት ተከታዮችን፣ ጎሣዎችንና ብሔረሰቦችን ያቀፈችው ደቡብ-አፍሪቃም አዲስ ሥርዓት ሲመሠርቱ ትኩረታቸው ባለፈው ሰቆቃና በሚያለያያቸው ላይ ሣይሆን በአንድነታቸው ላይ እንዲሆንና የማይለያየውን የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን ለመወሰን የያዙት ሕገ-መንግሥት የሚጀምረው "እኛ የደብ-አፍሪቃ ሕዝብ… We, the people of South Africa, ..)" በማለት ነው፤

መ) ጎሣንና ሐይማኖትን መሠረት ባደረገ ቀውስ የታመሰችው ናይጀሪያ ሕገ-መንግሥቷ የሚጀምረው "እኛ የናይጀሪያ ፌዴራል ሪፓብሊክ ሕዝብ…( We the people of the Federal Republic of Nigeria,..)" በሚል ነው፡፡ የኬንያም፣ የራሽያም፣ የኪዩባም፣ የቻይናም ሆነ የቬየትናም፣ ወዘተ.. ሕገ-መንግሥት የሚጀምረው እንዲሁ የሕዝባቸውን አንድ መሆን በማሣየት ነው፡፡ ታዲያ የኛዎቹ ጉዶች ከየት አመጡትና ነው የዜጎችን የሉዓላዊነት መብት ደምስሰውና ሕዝብን አንድ ሳትሆን የተለያየህ ነህ በማለት በስንት መስዋዕትነት የተገነባን

አንድነት በትነው ለመሰብሰብና ቀደው ለመስፋት የሚከጅሉት? ይኸን የሕዝባችንን ኢትዮጵያዊ ማንነት ያሳጣ በታኝ መንደርደሪያ በቅጡ ሳናገናዝብስ ስለ ሌሎቹ ብዙ ማለት ትርጉም ይኖረዋል ወይ?

እንደሚታወቀው ይኸንን "ሕገ-መንግሥት" በተመለከተ በተቃዋሚው በኩል የኢሕአዴግ ቁንጮዎች ያን ያደረጉት ለጊዚያዊ የፖለቲካ ጠቀሜታ ነው ከሚለው ጀምሮ በተለይ የጣልያን ባዕዳንን እቅድ የተከተለ የአገር አስተዳደራዊ አከፋፈል ስለሆነ የለየለት የጠላት ሥራ ነው፣ ወዘተ የሚሉ ትችቶች ሲሰጡ ቆይተዋል። የሆነ-ሆኖ የኢሕአዴግ መሪዎች ይኸንን መንገድ የተከተሉት በቀና መንፈስ በጎ ያደረጉ መስሏቸውም ይሁን ሆን-ብለው ያድረጉት፤ ይኸ ሰነድ ለአገዛዙ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር መርኃ-እቅዶች ዋነኛ ሽፋን፣ መከለያና ማስፈጸሚያ በመሆን ከጦርና ከፖሊስ ኃይሉ ባልተናነሰ በመሣሪያነት አገልግሏል። እየጠበበች በመጣች ዓለም የሚኖሩ ቀጣይ ትውልዶች ይኸ ሉዓላዊነታቸውን የጣሰና አንድነታቸውን የናደ "ሕገ-መንግሥት" ተግባራዊ እንዲሆን በመደረጉ በግብዝነታችን የቱን ያኸል እንደሚያዝኑና ትርጉም እንደሚያጡበት መገመት አያዳግትም። የሚገርመው ግን በዚኸ "ሕገ-መንግሥት" ላይ ቅሬታ፣ ነቀፌታና ተቃውሞ ከሚያሰሙ ወገኖች በኩል ከተወሰኑ ክፍሎች በስተቀር የሰነዱን እንከንና አደጋ በማመላከቱ ረገድ ዋነኛ ተጠቃሽ ሆና የምትቀርበው "አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ" ናት። እንደ እውነቱ ከሆነ ከዚኸ ሰነድ ውስጥ ለአገዛዙ መሪዎች መሰል-የሌለው አገልግሎት የሰጠቻቸው - ሥልጣን ዝንታለም ከአንድ ድርጅት (ከገዥው-ፓርቲ) እጅ እንዳይወጣ ሙጥጥ አድርጎ ካሸከማቸው ከአደገኛው 'አንቀፅ አምሣ' ጭምር የበለጠ ፣ በባለ-ሁለት በኩል ስለታማዋ "አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ" ናት ማለት ይቻላል።

ይኸን መሰል ድንጋጌ በሕገ-መንግሥቱ ያስቀመጠ ከኢትዮጵያ ሌላ አገር የለም። ይቺን አንቀፅ በተመለከተ ከሁሉ በፊት ግልጥ መሆን ያለበት አንድ ነገር አለ። ያም በአለው ተጨባጭ ሁኔታ አንቀፅዋን በተግባር መተርጎም ወይም አገር እንድትበተን ከፈለገ ሌላው ተግባራዊ እንዲያደርግ ዋና አስፈፃሚ መሆን የሚችል አንድ ኃይል ብቻ ነው። ያም ኃይል የአቶ መለስ/ስብሐት/ሥዩም/ዓባይ ፀሐዬ ሕወሓት ብቻ ነው። ይኸ ሃቅም ብዙዎች እነኝኸ ግለሰቦች የሚመሩት ቡድን ከትግራይ ሕዝብ ምኞት፣ ፍላጎትና አሣብ ውጭ ትግራይን ከቀረው ኢትዮጵያ ለመገንጠል ያላቸውን የቆየ ውስጠ-እቅድ ማረጋገጫ እንደሆነ ይጠቁማሉ። ለዚኸ እኩይ ዓላማና ምኞት ሁኔታም ይኸች ባለ-ሁለት-ጎን-ስለት አንቀፅ ለአገዛዙ ድርብ አገልግሎት መስጠቷን ቀጥላለች፤ አገልግሎቷም አዘናጊነት፣ አታላይነትና አነሁላይነት ነው። አነሁላይነቷም ለአገዛዙን ደጋፊዎችም፣ ለተቃዋሚውም ለሁለቱም ነው። አንቀፅዋን ከሕወሓት ሌላ በተግባር ሊተረጉማት እንደማይችል ለምሣሌ በ"ሽግግሩ" ጊዜ በምርጫ አቸንፎ የ"ሶማሊ ክልል መንግሥት" የተባለውን ይመራ የነበረው "የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ-አውጭ ግንባር (ONLF) የተሰኘው ድርጅት ሕዝበ-ውሳኔ (Referendum) በማድረግ አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝን ተጠቅሞ የመገንጠል ዓላማውን እውን ለማድረግ ያደረገው የረቀረ ሙከራ አለመሣካቱ ነው። ያ አካሄድ የአገዛዙን መሪዎች ምን ያኸል አጣብቂኝ ውስጥ ያስገባ ፈተና እንደነበር ግልጥ ነው። ቢፈልጉ ግን (ቢያደርጉት በነሱ ላይ የሚያስከትለው ምላሽ ቀላል ባይሆንም ቅሉ) ማድረግ ይችሉ ነበር። እንደሚታወቀው ግንባሩ በሕዝበ-ውሳኔ መንደርደሪያነት "አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝን" ተጠቅሞ ለመገንጠል የነበረውን እቅድ እውን ማድረግ ባለመቻሉም ነበር ዓላማውን ለማሣካት ትጥቅ ማንሣት ምርጫው የሆነው።

ይኸ "ሕገ-መንግሥት" በሥራ ላይ ከዋለ ጀምሮ የአንቀፅዋን አገር የመበተን አደገኝነት አበክሮና አምርሮ ያላቀረበና ያልሰበከ ተቃዋሚ የለም። ቀደም-ሲል በኢዴኃቅ ከዚያም በኅብረቱ (ኢዴኃኅ) የሰነዱን አጠቃላይ አደገኛነት ለማሣየት ጥረት ከመደረጉ ውጭ አብዛኛው በዚኸ ሰነድ ላይ የሚሰማና የቀረበ ትችት ሁሉ በዚችው አዘናጊና መሰሪ "አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ" ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ይታወቃል። ስለሆነም የአገዛዙን የፖለቲካ ፍልሥፍና፣ ይዞታና አካሄድ የማይደግፈውም ይሁን ለለውጥ የቆመው የተደራጀ ኃይል ትኩረቱን በዚች መዘዘኛ አንቀፅ ላይ በማድረግ ተራራ የመግፋት ሙግቱን በመቀጠሉ፤ አንድም

በተቃዋሚው ጎራ በተሰለፉ ኃይሎች መኻል አደረጃጀታቸው ይሁን የፖለቲካ ፍልሥፍናቸው ከአገዛዙ ያልተለየ በሆኑት ወገኖችና በአገሪቱ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ በሚታገለው አገር-ወዳድና ዴሞክራት የአንድነት ኃይል መኻል ያለው የነጠረ የግብ (የስትራቴጅ) ልዩነት በሽፍንፍን እንደተድበሰበሰ ይስሙላዊ አብሮ-የመቆም ይዞታ እንዲቀጥል አድርጓል። በተጨማሪም በተቃዋሚው ጎራ የተሠለፈው ወገን ይኸን “ሕገ-መንግሥት” በተመለከተ ያለውን ትኩረት በዚች አንቀፅ አደገኛነት ላይ እስከጣለ ድርስ የሚያቀርበውን የለውጥ አጀንዳ አገዛዙ አዙሮ “የብሐሔር/ብሔረሰቦችት” መብት ለምን እውቅና አገኘ ብላችሁ ነው የምትጮሁት በማለትና በማደናገር በአንድነት ኃይሉና በብሔረሰብ በተደራጁት መኻል ቅራኔ እንዲፈጠር ቢያንስ መጠራጠር እንዲኖር አስችሎታል። ያ ሲሆን ደግሞ ተቃውሞው ጥንካሬ እንዲጎድለው አስተውዋፅዖ ያደርጋል። ተቃዋሚው በዚች ተፈፃሚነቷ ከነአቶ መለስ ድርጅት ውጭ የመሆን ዕድል በሌላት አንቀፅ ላይ መረባረቡን ደግሞ አገዛዙ አጥብቆ ይፈልገዋል። ለምን ቢሉ፤ ለለውጥ ፈላጊው አገር-ወዳድና ዴሞክራት የአንድነት ኃይል በዋና የመታገያ ነጥብነት (አጀንዳነት) የትም የማይወስድና አዘናጊ ነጠላ ጉዳይ በመሆኑና አልፎም ያ ዓይነት በዚች ነጥብ ላይ ያተከረ አካሄድ በግልባጩ አገዛዙን“ወዳጅ-መግዣ” አድርጎ ስለሚጠቀምበት ነው።

ከሁሉም ከሁሉም ይኸች ጠንቀኛ አንቀፅ ለአገዛዙ የሰጠችው መሰል የሌለው አገልግሎት የፖለቲካ ጎሠኝነት ፍልሥፍና የተጠናወተውን ሠፈር “ላም-አለኝ በሰማይ” ዓይነት አጉል ተስፋ በመስጠት ማጃጃል መቻሏ ነው። አገዛዙ የሚከተለው የክልል አወቃቀር በነሱ አባባል “የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን” መብት ለማስከበር ነው የሚለውን አጥብቆ በመስበክና በተለይ የፖለቲካ ጎሠኝነት የተጠናዎታቸውንና ነገሮችን ሁሉ ከዚያ አንፃርና በዚያ መነጽር ብቻ የሚያዩ ክፍሎች ሠልፋቸውን ከነሱ ጎን ከማድረግ ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ለማረጋገጥ “ለማንነታችሁ እውቅና መስጠት ብቻ ሣይሆን ብትፈልጉ መገንጠል እንደምትችሉ በሕገ-መንግሥት ደንግገን ሰጥተናል፣.. ይኸንን መብታችሁን በመፍቀዳችንም ነው ይኸው 'ጨቋኞችና ትምክኅተኞች' የሚቃወሙን፣ ወዘተ” በማለት ስለሚሰብኩ፤ ይኸንንም መሥመር በበታች ሽሪክነት የሥልጣን-ተጋሪ በመሆን አገዛዙን በምስለኔነት የሚያገለግሉ ወገኖች የየ“ክልላቸውን” ሕዝብ “ይኸ መንግሥት የውስጥ አስተዳደራችን ባለቤቶችና ባለጉዳዮች እኛው እንድንሆን አስችሏል፣ መብታችንን አስከብሮልናል፣ ወዘተ. ” በማለት ተሞኝተው በማሞኘት የአገዛዙ አጋር እንዲሆኗቸው አስችሏል። ዕውነቱ ግን የእያንዳንዱ ክልል ሕዝብ ከሌላው የአገሪቱ ዜጎች ጋር ያለውንና ሊኖር የሚገባውን አንድነት እንዲያጣ፣ ተለይቶ እንዲኖርና ተለያይቶ እንዲያድግ ያደረገ፤ የይስሙላ የክልል መንግሥት የተባለውን ሥልጣንም በዋናነት የራሣቸው የድርጅት ሰዎች ከኋላ ሆነው ሆኖም ግን ለይስሙላ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑትን የአገዛዙ የፖለቲካ አቀንቃኞች (ካድሬዎች) በምስለኔነት ከፊት አሰልፎ የሚመራና የአገዛዙን እንጂ የኗሪውን ሕዝብ ጥቅም የማያስከብር እንደሆነ ይታወቃል። የየትኛው “ክልል” ሕዝብ ነው ያለ ገዥው ፓርቲ ጣልቃ ገብነት በሙሉ ነፃነት እራሱ በመረጣቸው የሚተዳደር?

በዚኸ መልክ “አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ” የዚኸ “ሕገ-መንግሥት” አደገኛና መዘዘኛ መሆን ብቻ ሣይሆን የአገዛዙን ተቃዋሚም ደጋፊም በተለያየ መልክ ሆኖም በእኩል አዘናጊና አታላይ ገፅታዋ አነሁላይ በመሆን ማገልገሏን ቀጥላለች። የ“አንቀፅ ሠላሣ-ዘጠኝ” አነሁላይነት ሊያከትም የሚችለው ሕዝባዊ ትግሉ ያልተከፋፈለ ትኩረቱንና ያልተበተነ አቅሙን አዲስ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ማስገኘት በማስቻሉ ንጥጥር ላይ አሣርፎ ሲቀጥል ብቻ ነው። ለማንኛውም መፍትኄው በአዲስ ቅኝትና በቁርጠኝነት በጋራ መቆም ብቻ ነው።

ኧረ እየተስተዋለ ወገን!

*ታኅሣስ ሁለት-ሽህ-ሦስት ዓ/ም*